## የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት (Lesson Planning)

1. አስፈላጊነት

- በመምህራን ላይ የሚስተዋለውን የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ክፍተቶች ለመሙላት እና

ሌሎች መካተት ያለባቸውን ጉዳዮች ማለትም

- የይዘት አስፈላጊነት(Rationale of the content)፣
- ተማሪዎች ከአካባቢያቸው እና ከቀዳሚ ክፍሎች ተምረዋቸው እና አዉቀዋቸው የሚመጡትን ዕውቀት (Pre-requisite knowledge) እና
- ተማሪዎችን እንደ ፍላጎታቸዉና ችሎታቸዉ ለማስተናገድ የሚያስችል የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት እንዲኖር ለማድረግ

2. ዓላማ፣

- በመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት አስፈላጊነትን በዉል ተረድተዉ በመምህራን ላይ ያለዉን የተሳሳተ አመለካከት ያስተካክላሉ፣
- የመማር ማስተማር ዓመታዊ/ ዕለታዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ መካተት ያለባቸዉን የትኩረት

ነጥቦች በመዘርዘር ናሙና የትምህርት ዕቅዶችን ያዘጋጃሉ፣

3. ይዘቶች፣

- የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት
- መርሃ ትምህርት
- ዓመታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት
- ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት

4. የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት

4.1. የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት ምንድን ነዉ?

- ስለምናስተምረዉ ትምህርት አስቀድመን በማሰብ የምንዘጋጅበት፣ የምናደራጅበት እና ሥራችን የታሰበዉን ግብ እንዲመታ የምናቀናብርበት ሂደት ነዉ።

4.2. የመማር ማስተማር ዕቅድ ማቀድ ለምን ይጠቅማል?

- ግልጽ የሆኑ ዓላማና አቅጣጫን በማስቀመጥ አስፈላጊ ያልሆኑ ክንዉኖችን ያሥወግዳል፣ የተፈቀደዉን ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም፣ በመምህራን ዘንድ በራስ መተማመንን ይፈጥራል ( መምህራን ምን፣መቼ እና እንዴት ማድረግ እንዳለባቸዉ አስቀድመዉ እንዲያዉቁ ያስችላል።)
- ተማሪዎች በመምህራን ላይ አመኔታ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፣
- በክፍል ዉስጥ ዲስፕሊን ለማስጠበቅ ይረዳል፣

4.3. ማቀድ ለምን ይጠቅማል?...

- የሱፐርቫይዘሮችን ሥራ ያቃልላል።
- የምዘናና ግምገማ ሥራን በአግባቡ ለመተግበር ያስችላል፣
- በአጋጣሚ ወይም በድንገት ሥራዉ በሂደት ላይ እያለ ቢቋረጥ ሥራዉን እንደገና ለማስጀመር ይጠቅማል።
  - ❖ በአጠቃላይ መምህራን ለማስተማር ወደ ክፍል ከመግባታቸዉ በፊት በአግባቡ የተዘጋጀ ዕቅድና በቂ ዝግጅት ሊኖራቸዉ ይገባል።
  - ❖ ያለዕቅድ መሥራት በጭፍን እንደመጓዝ ያስቆጥራል።

5. መርሃ ትምህርት

5.1. መርሃ ትምህርት ምንድን ነው?

- መርሃ ትምህርት ስለአንድ የትምህርት ዓይነት ምን (ይዘት)፣ እንዴት (ሥነ-ዘዴ)፣ ለምን ዓላማ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደምናስተምራለን ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።
- በተጨማሪ ከተማሪዎች በዝርዝር ምን እንደሚጠበቅ እና ምን ያህል እንዳወቁ የመመዘኛ ሥልቶችን ይጠቁማል።

5.2. የመርሃ ትምህርት ጠቀሜታ

- ለብሔራዊና ክልላዊ ፈተናዎች እና ለመማሪያ-ማስተማሪያ መጻህፍት ዝግጅት መነሻ ሆኖ ያገለግላል፣

- ለዓመታዊ/ ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት መነሻ ሆኖ ያገለግላል፣
- የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ፍላጐት እንድናሟላ ያግዛል፣
- መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ ማድረግ ያለባቸውን ጥንቃቄያስረዳል፤
- ስህተቶችንም እንዲቀንሱ ያግዛል፣
- ለመምህራን አንድን የትምህርት ይዘት እንዴት እንደሚያስተምሩ፣
- የትኛው የመማር-ማስተማር ስነ-ዘዴ ለይዘቱ የተሻለ እንደሆነ፣
- ከይዘቱ ጋር ተስማሚ የሆነዉን የምዘና ዘዴ ያመላክታል፡፡

5.3. መርሃ ትምህርት በዉስጡ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- የክፍል ደረጃውን አጠቃላይ ዓላማ
- ይዘቶችና ንዑስ ይዘቶች
- ለእያንዳንዱ ምዕራፍ እና ይዘት የተመደበ የክፍለ ጊዜ ብዛት
- የእያንዳንዱ ምዕራፍ ዓላማዎች
- የእያንዳንዱ ይዘት /ንዑስ ይዘት ዝርዝር ዓላማ
- የማስተማር ስነ-ዘዴዎች
- ሚዲያዎች
- ምዘና እና የመሳሰሉትን አካቶ ይይዛል፡፡

6. ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ

6.1. ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ ምንድን ነው?

- ዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ በአንድ የትምህርት ዓመት መሸፈን ያለባቸው በአንድ ትምህርት ዓይነት ውስጥ የሚገኙ ክፍለ ትምህርቶች ዝርዝር ተግባራት ድምር ነዉ፡፡

6.2. የዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ ጠቀሜታ፡

- ከየት ተነስተን የት እንደምንደርስ በማመላከት አቋራጭ መንገድን ለመወሰን ይረዳናል፣
- መምህራን የሚያስተምሩትን ይዘት ቀድመው እንዲላመዱት ያግዛል፣
- የይዘትን ቅርጽ፣ጥንቅር እና ቅደም ተከተልን ያሳያል፣
- ተማሪዎች በይዘቱ ላይ ስላላቸዉ የቅድሚያ ዕዉቀት (pre-requisite knowledge/skill of students) መምህራንን ያመላክታል፡፡
- ለእያንዳንዱ ተግባር የተሰጠውን ጊዜ በትክክል ለማወቅ ይረዳል፣
- የክፍለ ትምህርት ዕቅድ (Unit plan) እና ዕለታዊ የትም/ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይረዳል፣
- የት/ቤቱን የመማር ማስተማር መርሃ ግብር በአግባቡ እንዲፈፀም ይረዳል፣
- ዓመታዊ የሆኑ ምዘናዎችን መቼ እንደምናካሄድ ይጠቁመናል፡፡

6.3. የዓመታዊ የትምህርት ዕቅድ በዉስጡ የሚከተሉትን ያካትታል

6.3.1. የምዕራፉ አስፈላጊነት (Rationale of the unit)፡- ይህ ክፍል

- ምዕራፉ ከተማሪዎች የዕለት ዕለት ህይዎት ጋር ያለው ግንኙነትን፣
- ተማሪዎች ወደፊት ማጥናትና መሠማራት ከሚፈልጉት መስክ እና
- ለህብረተሰቡ ስለሚሠጠው ጠቀሜታ ጋር አያይዞን የምናብራራበት ክፍል ነው፡፡

6.3.2. ቀደሞ በተማሪዎች ሊታወቅ የሚገባ ዕውቀት/ ክህሎት (pre-requisite knowledge/skill of students)፡-በዚህ ክፍል ዉስጥ ተማሪዎች ከምዕራፉ ጋር በተያያዘ ያሏቸዉን ዕዉቀቶች የምንዘረዝርበት ሲሆን ዕዉቀቶቹን ከታችኞቹ ክፍሎች፣ ባለበት የክፍል ደረጃ በሌሎች ትምህርቶች ወይም በህይወት ተሞክሮወቻቸዉ ያገኙዋቸዉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

Format of annual plan (The academic year)

Name of teacher: _________ Name of school: ___________

Subject: _______________ Grade: ____________

Total number of allocated periods_____

Number of period per week_________

## 7. ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ

- ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ማለት በዕለቱ /ከክፍለ ጊዜዉ ትምህርት በኋላ በተማሪዎች ላይ ሊመጣ የተፈለገዉን ለዉጥ አስቀድመን የምንነድፍበትና ሊተገበሩ የታሰቡትን ክንዉኖች ወይም ተግባራት አስቦና አሰላስሎ በወረቀት ላይ ማዘጋጀት፣ ማደራጀትና መቀናበር ማለት ነዉ።
- ዕለታዊ የመማር-ማስተማር ዕቅድ በአንድ ቀን ለአንድ ክፍለ ጊዜ የሚቀርብ የትምህርት ይዘትን ማቀድ ነዉ።
- ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ለመማር-ማስተማር መጎልበት የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት።

ከእነዚህ ጠቀሜታዎች መካከል፡-

- የይዘቱን ዓላማ ዳር ለማድረስ ያስችላል፣
- በርካታ የመማር-ማስተማር ዘዴዎችንና ስልቶችን በሥራ ላይ ለማዋል ይጠቅማል፣
- የመማር-ማስተማር ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም ይረዳል፣
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ማቀድ መምህሩ/ሯን አስፈላጊ የመማር-ማስተማር ሚዲያ ለማሰባሰብና ለማዘጋጀት ይረዳል፣
- ተማሪዎችን በአግባቡ ለመመዘን /ለመገምገም ያስችላል፣
- ግልጽ የሆነ ዓላማና አቅጣጫን በማስቀመጥ አስፈላጊ ያልሆኑ ክንዉኖችን ያስወግዳል፣
- በመምህራን ዘንድ በራስ መተማመን ይፈጥራል፣
- ተማሪዎች የዕለቱን ትምህርት ፋይዳ ተገንዝበዉ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
- የዕለቱ ትምህርት ከተጠናቀቀ በኋላ የአፈጻጸም ዕብረቃ ላይ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ያለዉን ክፍተት በመለየት ለቀጣዩ ትምህርት ማስተካከያነት ይረዳል። ወዘተ…
- ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ የሚዘጋጀዉ ዓመታዊ ዕቅድንና የክፍለ ትምህርቱን ዕቅድ መሠረት በማድረግ ሲሆን በተጨማሪም የሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሎችን በመሠረታዊነት በአግባቡ መጠቀም ይኖርብናል።

### 7.1. ዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ በዉስጡ ምን ምን ነገሮችን ያካትታል?

Format of daily lesson plan

Name of teacher: _____Name of school: ____Subject:___

Grade and section: __

Date of lesson: ____Unit of lesson: ___Sub-unit of lesson: ____

Topic of lesson: ____Rationale of the topic: _________

Specific objectives: ______________________________

Prerequisite knowledge/ skill of students____________________

### 7.2. ዕለታዊ የመማር-ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት የትኩረት ነጥቦች የዕለታዊ ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚከተሉትን የትኩረት ነጥቦች ግምት ዉስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

1. የዕለቱን ትምህርት አስፈላጊነት መንደፍ (Generate the rationale of the lesson topic) ፣

ይዘቱ ከማህበረሰቡና ከተማሪዎች የዕለት ከዕለት ህይወት ጋር ያለዉን ግንኙነትና የተማሪዎች ይዘቱን መማር ያለዉን አስፈላጊነት በምሣሌ አስደግፎ በዕቅዱ ዉስጥ ማስቀመጥ ይገባል።

2. የመማር-ማስተማር ዝርዝር ዓላማዎችን መንደፍ፣ ዕለታዊ ትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ላይ የሚጻፉት ዝርዝር ዓላማዎች ናቸዉ። ከተማሪዎች የሚጠበቀዉን የባህሪ ለዉጥ ማመላከት ስላለባቸዉ የመማር ማስተማር ዝርዝር ዓላማዎች ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ላይ ሲሰፍሩ የሚከተሉትን ጉዳዮች መሠረት ማድረግ አለባቸዉ፡-

- በሚማሩት ጉዳይ ላይ የሚያተኩሩ (Specific)
- ሊለኩ የሚችሉ (Measurable)
- ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ (Achievable)

- እርግጠኛነትን የሚያጎናጽፉ (Realistic)
- በጊዜ የተወሰኑ (Time bound) መሆን አለባቸዉ።

3. ርዕሶችን መምረጥ

- በዕለታዊ የመማር ማስተማር ዕቅድ ዝግጅት ወቅት ርዕሶችና ንዑሳን ርዕሶች የሚወሰዱት ተዘጋጅተዉ ከሚላኩ የሥርዓተ-ትምህርት ማቴሪያሎች ዉስጥ ነዉ።ሆኖም እነዚህ ርዕሶች አካባቢያዊ ገጽታ እንዲኖራቸዉና ከተማሪዎች ልምድ ጋር አቆራኝቶ ለተማሪዎች የማቅረብ ጥበብ ያለዉ ከመምህራን ዘንድ ነዉ። ስለዚህ ለዕለቱ የሚቀርበዉ ርዕስ በጥንቃቄ ከተማሪዉ መጽሀፍ ከተወሰደ በኋላ፣ ተማሪዎች ከሚማሯቸዉ ሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ሊኖራቸዉ የሚችለዉን ጎናዊ ቅንጂት (horizontal connection) በሚገባ ማጤን፣ ዋናዉ ርዕስ ከንዑሳን ርዕሶች ጋር ተያያዥነት እንዳለዉ በማረጋገጥ፣ መምህሩ/ሯ እና ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ ሊያሣትፍ በሚችል መልኩ መታቀድ አለበት።

4. የሚከናወኑ ተግባራትን በጥንቃቄ መቅረጽ የሚከናወኑ ተግባራትን ከዕለቱ ትምህርት ርዕስ ጋር በሚስማማ መልኩ ተመርጠዉ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅዱ ላይ ሊጻፉ ይገባል። ተግባራቱም ሲቀረጹ የተማሪዎቹን ተሳትፎ በይበልጥ እንዲያመላክቱ ሆነዉ መቀመጥ አለባቸዉ።
5. ተስማሚ የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎችን መምረጥ፣ ተገቢ የሆኑ የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎችን ማዘጋጀት ለዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ጠቀሜታዉ ከፍተኛ ነዉ። በመሆኑም ለዕለቱ የትምህርት ርዕስና ለንዑሳን ርዕሶች ተስማሚ የሆኑ ችግር ፈችና አሳታፊ ሥነ-ዘዴዎችን አስቀድሞ ማቀድ ያስፈልጋል። ሥነ-ዘዴዎች ተማሪዎችን የሚያሳትፉ፣ ተማሪዎች ፈልገዉና ተመራምረዉ እንዲያዉቁ በተግባራዊ ክንዋኔዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ዕድል የሚሰጡና የመምህራንን የማመቻቸት ሚና የሚያጎሉ ሊሆን ይገባል።
6. ተገቢ የመማር-ማስተማር ሚዲያዎች /መርጃ መሳሪያዎችን/ ማዘጋጀት፣ መምህራን ዕለታዊ የመማር-ማስተማር ዕቅድን ሲያዘጋጁ ብርቱ ጥንቃቄ ሊያደርጉባቸዉ ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች አንዱ የመማር-ማስተማር ሚዲያዎችን ማዘጋጀትና መምረጥ ነዉ።

   የመማር-ማስተማር ሚዲያዎች ለመማር-ማስተማር ሂደት ህይወት የሚሰጡና ተማሪዎች <u>አምስቱን አባላተ ስሜት</u> ተጠቅመዉ እንዲማሩ ይረዳሉ።

7. ተስማሚ የምዘና ስልቶችን መምረጥ፣

በዕለቱ ትምህርት ተማሪዎች የሚጠበቀዉን የባህሪ ለዉጦች ማምጣታቸዉን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የተለያዩ ምዘና ስልቶችን በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ማካተትና መጠቀም ያስፈልጋል።

ለምሳሌ፡- ምልከታዎች፣ የቃል ጥያቄዎች፣ የክፍል ሥራዎች፣ የቤት ሥራዎች፣ ቴስቶች ወዘተ… የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ለመመዘን የሚረዱ የምዘና ስልቶች ናቸዉ።

8. ለተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ (Learner support)፣ ሁሉንም የክፍሉ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ ወቅት እኩል ተጠቃሚ ለማድረግ ለአካል ጉዳተኛ፣ ለፈጣን፣ ለመካከለኛና ዝቅተኛ አቀባበል ላላቸዉ ተማሪዎች ሊደረጉ የታሰቡ ድጋፎችን በዝርዝር በዕቅዱ ዉስጥ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

- ለተማሪዎች የሚደረግ ድጋፍ (Learner support)…

ለአብነት፡-

- የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን አፈጻጸም በቅርብ መከታተልና ፍላጎታቸዉን በመለየት ትምህርታቸዉን መደገፍ፣
- ለፈጣን ተማሪዎች ስለይዘቱ በተጨማሪ የሚያነቡዋቸዉን መጻህፍት ማመላከት፣
- ዝቅተኛ አቀባበል ያላቸዉን ተማሪዎች ክፍል ዉስጥ በቅርብ መከታተልና መደገፍ እንዲሁም ተጨማሪ እገዛ ከክፍል ዉጭ ማድረግ።

አመሰግናለሁ


ቆጣሪ የመጀ/ደ/ት/ቤት

የመምህራን ልማት ም/ር/መ/ር ዳዊት ፋንታሁን 2015 ዓ.ም